# ምንደኛ ፡ አበባው

አሽከር ፡ አበባው ፡ ናልኝ
ቅጥረኛው ፡ ናልኝ
አንጃን ፡ ይዘህልኝ ።
　　አሽከር ፡ አበባው ፡ ናልኝ
　　ቅጥረኛው ፡ ናልኝ
　　አንጃን ፡ ይዘህልኝ ።

አንጃና ፡ ቅጥረኛን ፡ አበባው
　　አደራጅተህ ፡ ጠብቅ....
ገንዘብ ፡ ካስፈለገህ ፡ አበባው
　　ከኢምባሲ ፡ ጠይቅ....
ክፉ ፡ አውራ ፡ ስለኔ ፡ አበባው
　　እንዳትጠረጠር...
ሚስጥሩ ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ አበባው
　　ሸውዶ ፡ ለማደር ....

　　አሽከር ፡ አበባው ፡ ናልኝ
　　ከሃዲው ፡ ናልኝ
　　ሴራው ፡ ይስመርልኝ ።
አሽከር ፡ አበባው ፡ ናልኝ
ከሃዲው ፡ ናልኝ
ሴራው ፡ ይስመርልኝ ።

ክፈላቸው ፡ በዘር ፡ አበባው
　　በስውር ፡ ሳያውቁ....
ተገንጣይ ፡ ጠባቦች ፡ አበባው
　　አላግባብ ፡ ተጠቁ....
አንተም ፡ አውግዝ ፡ እኔን ፡ አበባው
　　ብልጦች ፡ እንዳይነቁ
ኢትዮጵያዊነትን ፡ አበባው
　　ሳያውቁ ፡ እንዲለቁ....
በምነታቸው ፡ ዝመት ፡ አበባው
　　በሃይማኖታቸው....
ባላሙዲን ፡ ዶላር ፡ አበባው
　　ወስደህ ፡ ጥመቃቸው....

　　አሽከር ፡ አበባው ፡ ናልኝ
　　ምንደኛው ፡ ናልኝ
　　አላንተ ፡ አይሆንልኝ ።
አሽከር ፡ አበባው ፡ ናልኝ
ምንደኛው ፡ ናልኝ
አላንተ ፡ አይሆንልኝ ።

አንድነት ፤ አንድነት ፤ አበባው
እያልክ ፤ ስበካቸው…
ቢኖሩም ፤ ባይኖሩም ፤ አበባው
ቁጥር ፤ አብዛላቸው…
እንደምንም ፤ ብለህ ፤ አበባው
ተስፋ ፤ አስቆርጣቸው…
ኢትዮጵያ ፤ የሚለውን ፤ አበባው
በለው ፤ ትምክህተኛ…
እንዳያዝን ፤ ብቻ ፤ አበባው
ተገንጣይ ፤ ዘረኛ ።

አሽከር ፤ አበባው ፤ ቅጥር
ክደቱ ፤ ቅጥር
ና ፤ የኔ ፤ ሽቅርቅር ።

        አሽከር ፤ አበባው ፤ ቅጥር
        ክደቱ ፤ ቅጥር
        ና ፤ የኔ ፤ ሽቅርቅር ።

ታዛቢው